# በገዢው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ
# <u>አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 27/2002</u>

የፌዴራል፣ የክልል እና የከተማ አስተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የዕቃና የአገልግሎት ግዥ በሚፈፅሙበት ጊዜ የሚከፍሉት የተጨማሪ እሴት ታክስ በትክክል ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ እንዲሆን ለማስቻል የታክሱ ሂሳብ ግዥውን በሚፈፅሙት መሥሪያ ቤቶች ተይዞ ለታክሱ ባለሥልጣን የሚተላለፍበት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ይህ ሥርዓት ከመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሰበሰቡትን ታክስ ይዘው የሚሠወሩትን ሕገ-ወጦች በመከላከል የታክሱ ሂሳብ በተገቢው ጊዜና መጠን ተሰብስቦ ገቢ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል መሆኑ ስለታመነበት፣

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 609/2001 አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 5 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ «በገዢው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም የወጣ መመሪያ ቁጥር 27/2002» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. <u>ትርጓሜ</u>

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፣

1. «ታክስ» ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው።

2. «አዋጅ» ማለት የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 (እንደተሻሻለ) ነው።

3. «በገዢው ተይዞ የሚከፈል ታክስ» ማለት በአዋጁ አንቀጽ 7(5) በተደነገገው መሠረት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ሲከናወን ሊከፈል የሚገባ እና በገዢው ተይዞ ለባለሥልጣኑ ገቢ የሚደረግ የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው።

4. «ወኪል» ማለት ታክስ በሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፍል የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ይዞ ለታክስ ባለሥልጣኑ ገቢ የሚያደርግ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው።

5. «ደረሰኝ» ማለት ታክሱን ቀንሰው የሚያስቀሩ ወኪሎች በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዕውቅና የሚያሳትሙት እና ታክሱ ተቀንሶ ለመቅረቱ ማረጋገጫ እንዲሆን የሚሰጡት፣ የተያዘውን ታክስ መጠን የሚያሳይ ሰነድ ነው።

6. «ባለሥልጣን» ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና የክልል መንግሥታት እንዲሁም የከተማ አስተዳደር ገቢ ሰብሳቢ መሥሪያ ቤቶች ናቸው።

7. «ሚኒስቴር» እና «ሚኒስትር» ማለት እንደቅደም ተከተሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር ነው።

8. በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉና በአዋጁ የተተረጎሙ ቃላትና ሐረጎች በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ መመሪያ የፌዴራል፣ የክልል መንግሥታትና የከተማ አስተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በሚያከናውኑት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም የክልል መንግሥታትና የከተማ አስተዳደር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና የልማት ድርጅቶች ከሚፈፅሙት ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ታክሱን ቀንሰው መያዝ የሚጀምሩበት ጊዜ ወደፊት ሚኒስትሩ በሚያስተላልፈው ሴርኩለር ይወስናል፡፡

## 4. ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ላይ ተቀናሽ ተደርጐ ስለሚያዝ ታክስ

1. ማንኛውም ወኪል በሚፈፅመው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ለአቅራቢው መክፈል የነበረበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ በማስቀረት በየወሩ ቀንሶ ያስቀረውን ታክስ በሚቀጥለው ወር ውስጥ በታክስ ከፋይነት ለተመዘገበበት የታክስ ባለሥልጣን ገቢ ያደርጋል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ተቀንሶ የሚቀረው ታክስ በቅድሚያ ክፍያና በከፊል በሚደረጉ የአገልግሎት ወይም የዕቃ አቅርቦቶች ክፍያዎች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ የተደነገገው ቢኖርም በቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት ላይ የሚሰበስብ የተጨማሪ እሴት ታክስ በገኘው አይያዝም፡፡

## 5. ታክሱ ተቀናሽ የሚደረግበት ግብይት ዋጋ

1. በዚህ መመሪያ መሠረት ወኪሉ ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ላይ የታክሱን ሂሳብ ተቀናሽ የሚያደርገው የአንድ ጊዜ ግብይት ዋጋ ከብር 5,000 (አምስት ሺህ) በላይ ሲሆን ነው፡፡ የግብይቱ ዋጋ ብር 5,000 እና ከዚያ በታች ከሆነ ወኪሉ የታክሱን ሂሳብ ጭምር ለታክስ ከፋዩ መክፈል ይኖርበታል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ሰው ወይም ድርጅት በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡ ስለሆነም የገንዘቡ መጠን ከግምት ውስጥ ሳይገባ የታክሱ ሂሳብ ተቀናሽ መደረግ አለበት፡፡

## 6. የወኪል ግዴታ

ማንኛውም ወኪል፡-

1. ይህ መመሪያ በሥራ ላይ ከሚውልበት ቀን በፊት በታክስ ባለሥልጣኑ ተመዝግቦ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ሰርተፊኬት የመውሰድ፣

2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5(1) ከተጠቀሰው በስተቀር በሚፈፅመው በእያንዳንዱ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ ሂሳብ ቀንሶ የመያዝ፣

3. ከእያንዳንዱ ታክስ የሚከፈልበት ግብይት በሚይዘው ታክስ መጠን ልክ ለዕቃ ወይም ለአገልግሎት አቅራቢው ደረሰኝ የመስጠት፣

4. በወሩ ውስጥ ካከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ቀንሶ የያዘውን ታክስ ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለታክስ ባለሥልጣኑ ገቢ የማድረግ፣

5. ታክስ ከሚከፈልበት ግብይት ጋር በተያያዘ ክፍያ የተፈፀመለትን ሰው ወይም ድርጅት ስም፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ቁጥር፣ የተፈፀመውን ግብይት ዋጋ እና ተቀንሶ የቀረውን የታክስ መጠን የሚያሳይ ዝርዝር ባለሥልጣኑ በሚያዘጋጀው ቅፅ ላይ ሞልቶ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ከሚያደርገው ሂሳብ ጋር የማቅረብ፣ ግዴታ አለበት::

## 7. ታክስ ስለማቀናነስ እና የተመላሽ ጥያቄ

1. ታክስ ተቀናሽ የተደረገበት ዕቃ ወይም አገልግሎት አቅራቢ ከወኪሉ በተሰጠው ታክሱ ተቀናሽ መደረጉን በሚያረጋግጠው ደረሰኝ ላይ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን በግብአት ላይ ለከፈለው ታክስ ማካካሻ ሊያውል ይችላል::

2. ዕቃ ወይም አገልግሎት አቅራቢው የታክሱ ሂሳብ ተቀናሽ ተደርጐ የተሰጠውን ዋናውን ደረሰኝ ታክሱን በሚያስታውቅበት ጊዜ ለባለሥልጣኑ ገቢ ማድረግ አለበት::

3. ታክስ ከፋዩ ታክስ የሚከፈልበትን ግብይት በሚያከናውንበት ጊዜ በተቀበለው ደረሰኝ የተመለከተው የገንዘብ መጠን ለሁለት ወራት በግብአት ላይ ከተከፈለ ታክስ ጋር እንዲካካስ አድርጐ በደረሰኙ ላይ የተመለከተው የገንዘብ መጠን በግብአት ላይ ከተከፈለው ታክስ የበለጠ ሆኖ ከተገኘ ታክስ ከፋዩ የተመላሽ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል::

4. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የቀረበውን ጥያቄና የታክስ ከፋዩን ሂሳብ መርምሮ ጥያቄው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ሊደረግ የሚገባውን ሂሳብ መመለስ አለበት::

## 8. ተቀናሽ የተደረገውን ታክስ ገቢ ስለማድረግና ስለማከፋፈል

1. ታክስ ቀንሶ የመያዝ ግዴታ የተጣለበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት ቀንሶ የያዘውን ታክስ ገቢ የሚያደርገው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገበበት የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ይሆናል::

2. ታክስ ቀንሶ የመያዝ ግዴታ የተጣለበት የመንግሥት የልማት ድርጅት ቀንሶ የያዘውን ታክስ ገቢ የሚያደርገው የግብር/ታክስ ክፍያ ግዴታውን ለሚወጣበት የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት ይሆናል::

3. የክልል መንግሥታትና የከተማ አስተዳደር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በዚህ መመሪያ መሠረት ተቀናሽ ተደርጕ ገቢ የተደረገላቸውን ታክስ ተቀናሽ የተደረገበት ታክስ ከፋይ ለተመዘገበበት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት መላክ አለባቸው::

4. የክልል መንግሥታትና የከተማ አስተዳደር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ የተደረገላቸውን ታክስ ለሚመለከተው የታክስ ባለሥልጣን ሲያከፋፍሉ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ለሚቀረው ግብር አፈፃፀም ከተዘጋጀው ቅጽ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ቅጽ በመጠቀም ገንዘቡ ለተላከለት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት ሪፖርቱን በአንድነት መላክ አለባቸው::

## 9. ተቀናሽ ተደርጐ ለሚያዝ ታክስ የሚሰጥ ደረሰኝ

1. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ተቀናሽ ተደርጎ ለሚያዝ ታክስ የሚውል ደረሰኝ እንዲያሳትም ለወኪሉ ፈቃድ ይሰጣል::

2. ወኪሉ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት ደረሰኝ ያሳትማል:: ባለሥልጣኑ የሚያወጣወን የደረሰኝ አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓት ተከትሎ ደረሰኙን ጥቅም ላይ ያውላል::

3. ወኪሉ ተጨማሪ ደረሰኝ እንዲያሳትም የሚፈቀድለት ቀደም ሲል ባሳተመው ደረሰኝ ቀንሶ የያዘውን ታክስ በትክክል ለባለሥልጣኑ ገቢ ማድረጉ ሲረጋገጥ ይሆናል::

## 0. በገዥው ተይዞ የተከፈለውን ታክስ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ

ባለሥልጣኑ:-

1. ወኪሉ ያሳተማቸውን ደረሰኞች በመመርመር የታክሱን አሰባሰብ ትክክለኛነት ያረጋግጣል::

2. ወኪሉ በፈፀማቸው ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ላይ በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሠረት ታክሱን በትክክል ቀንሶ ያለማስቀረቱን ወይም የቀነሰውን ታክስ ለባለሥልጣኑ ገቢ ያለማድረጉን ሲያረጋግጥ በልዩነት የሚፈለገው ታክስ እንዲከፈል ያደርጋል::

## 01. የሂሳብ አመዘጋገብ

1. ተቀናሽ ሆኖ የሚቀረው ሂሳብ በተከፋይ የሂሳብ መደብ ቁጥር 5059 ይመዘገባል::

2. ወኪሉ በተከፋይ የተያዘውን ገንዘብ ለባለሥልጣኑ ገቢ ሲያደርግ የተከፋይ ሂሳብ ወጪ በሚል ይመዘግባል፤ ይህንኑም ለሚኒስቴሩ በየወሩ በሚያቀርበው የሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ያካትታል።

## 02. <u>አስተዳደራዊ መቀጫና የወንጀል ቅጣት</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 የተዘረዘሩትን ግዴታዎች ያልተወጣ ወኪል በአዋጁ እና በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 90 መሠረት አስተዳደራዊ መቀጫና የወንጀል ቅጣቶች ተፈፃሚ ይደረጉበታል።

## 03. <u>የመመሪያው ተፈፃሚነት</u>

ይህ መመሪያ ከመጋቢት 1 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

*አዲስ አበባ የካቲት 3 ቀን 2002 ዓ.ም*

*ሱፍያን አህመድ*
*የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር*

# በገዢው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈፃፀም የወጣ መመሪያ

*የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር*

*የካቲት 2002 ዓ.ም*

*አዲስ አበባ*

DirectivVAT/GT

# የሕግ አገልግሎት ደጋፊ የሥራ ሂደት የ2002 ግማሽ ዓመት የሠራተኞች ውጤት ተኮር ዕቅድ

# ለፌዴራል መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

*ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር*

***መጋቢት 2002***

DirectivVAT/GT

# የፌዴራል መንግሥት
# የግዥ አፈፃፀም መመሪያ

*የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር*

*ግንቦት 2002 ዓ.ም*